# አባ ስርጉት ሃብቴ



ጉንፋን መሳይ ይዞ፣ ብርቱ እያሳላቸው፣
እስቲ ምን ይባላል ቆላ መውረዳቸው፣
“ይሄ ቆላ መውረድ ይቅርብዎት” ብላቸው፣
የሰው ምክር መቸም አይሰሙም እሳቸው!
 ውሎ አደረና ሳሉ ጸናባቸው።

እስላሙን ላስተምር፣ ላጥምቀው እያሉ፣
ላይ ታች ቆላ ደጋ፣ አጉል ሲዋልሉ፣
በሰው ዓይን ገቡ፣ ከሰው እጅ ዋሉ።
የሰው ነገር ከንቱ፣ አያርፍም አመሉ፤
 ክብራቸው ተገፍፎ እጅጉን ቀለሉ።



የቆላ ንፋስ ነው በሳል መታመሙ፣
መስበክ፣ ማስተማርም ያለ ነው በዓለሙ!
አባ ስርጉት ሃብቴ በአዳል ሴት ታሙ፣
እስላም ነች ተባለ፣ አባም አሰለሙ…
 የሳምባ ነቀርሳ በረታ ሕመሙ።

ሰዉ ሲመክራቸው መች ይሰሙ እሳቸው!
አመለኛው እግር አላርፍ ብሏቸው፣
በጣም ያሳዝናል ይህ ሆነ ዕጣቸው፣
እጀግ ተዋረዱ፣ ቀኑ ሲጥላቸው፣
 አባም ወንድ ሆኑና አዳል ሰለባቸው!

ገ/ኢ. ጐርፉ።